ሚያዚያ 10 ቀን 2001 ዓ.ም.

<u>ከኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ተወካዮች የተሰጠ አጭር መግለጫ</u>

በመቻቻልና በመማማር በጋራ መስራት መቻል የወቅቱ የህዝባችን ቁልፍ ጥያቄ ነዉ።

ስለዚህ ሃገር የምትሻዉ የቆሸሹ እጆችን ሳይሆን የጸዱ አእምሮችን ነዉ። ነገር ግን የሰዉ ገንዝብ የለመደ ሹም የአህያ ስጋ የለመደ ጅብ አይቻልም ሆነ እና አቶ ስለሺ ጥላሁን የዓለም አቀፍ ኮሚቴዉ የድረጅቱ ጉዳይ ሃላፊ ሆነዉ እንዲሰሩ ብንመድባቸዉ ቀን ቀን አርበኛ ማታ ማታ ከዳተኛ ሆነዉ አግኝተናቸዋል።

እኛ ደግሞ በህዝብ ተመርጠን የህዝብ ድምጽ ከላያችን ሳይወርድ በእንደነዚህ ዓይነት ጠባብ ባላቸዉ ግለሰቦች ትግሉ ቅንጣት ታክል ፈቀቅ እንደማይል ታሪክ ምስክር ነዉ።

1. ለሙከራ ወደግንባር ባለፉት ወራት ከሌሎች ጋር እንዲሄዱ በዝግጅት ላይ እንዳሉ አቶ ስለሺ ከድተዉ ወደ አስመራ ሄደዋል።

2. ለሶስት ዓመታት ከግንባሩ ጋር ምንም ግንኙነት ከሌላቸዉ ግለሰቦች ጋር ሲሰሩ ቆይተዉ በቀጥታ እኛ በግንባር ተወክለን ወደ አዉሮፓ እንደመጣን በ 48 ሰዓት ተቀላቅለዉናል። እኛ ደግሞ ባለፈዉ ጉዳይ ላይ ለመነታረክ ጊዜ ስለሌለን ካለፈዉ ስህተታቸዉ ታርመዉ ይሰራሉ ብለን ነበር። ነገር ግን ግለሰቡ ቢያጥቡት ጭቃ ነዉና የግንባሩን ድህረ ገጽ እኔ እሰራዋለሁ በማለት እኛ ባላወቅነዉና ባልሰማነዉ ሁኔታ ደብቆ ወደ ለንደን በመዉሰድ አላስፈላጊ የግንባሩን መረጃዎች እንደፈለጉ እየለጠፉ አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን እንዲሸሹ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

ስለዚህ በሃገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ ሃገር ያላችሁ አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን ይህን የተሳሳተ አካሄድ የግንባሩ ወኪሎችም ሆን የዓለም አቀፍ ኮሚቴዉ የማይቀበለዉ መሆኑ እና አብረዉም እየሰሩ አለመሆኑን ስንገልጽ ግለሰቡም ለማን እየሰሩ እንደሆነ ስለማናዉቅ ማንኛዉም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በጥንቃቄ እንዲከታተለዉ በአክብሮት እናሳስባለን።

ከቀድሞዉ የቅንጅት አባላት የህዝብ ተመራጮች

አቶ ልዑል ቀስቅስ የግንባሩ ተውካይና የዓለም አቀፍ ኮሚቴ ሊቀመንበር
አቶ አሰፋ ሃይሉ የግንባሩ ተወካይና የዓለም አቀፍ የፖለቲካ ጉዳይ ሃላፊ

ግልባጭ፣ ለኢ.ህአግ ማእከላዊ ኮሚቴና ለግንባሩ ሊቀመንበር

አንድነት ሃይል ነዉ!

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር
ኢሕአግ
EPPF
Ethiopian People Patriots Front